
# ፈለገ ብርሃን

ልዩ ዕትም



# ጤናማ አገልጋይ



# ማውጫ



## ዋና አዘጋጅ
አንዋር አብራር

## ም/ ዋና አዘጋጅ
ጌታቸው በቀለ

## ከፍተኛ አዘጋጆች
ማርቆስ ሙሉጌታ
ማስታወሻ መዝገቡ
ደጋረገ መንግስት
ኢሌኒ ፈቃዱ
ተሬሳ ጫልችሳ
ቃለ ክርስቶስ ታደሰ

## ካሜራ ባለሞያ
ቢኒያም ብርሃኑ
አወል ሃሰን
ምናሴ ዬሴፍ


የዋና ሥራ አስፈጻሚ መልዕክት 06
የሠራተኛ ማኅበር ሊቀ መንበር መልዕክት 08
የሰው ሃይል ሥራ አስፈጻሚ መልዕክት 10
የዓለም ኤድስ ቀን መሪ ቃል 12
በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ቢሮ የተከናወኑ አንኳር ተግባራት 14
ኤች.አይ.ቪኤድስ እና አሁናዊ ሁኔታው 18
የኤች.አይ.ቪ ኤዲስ መተላለፊያ መንገዶች 22
የሥራ ላይ ደህንነት ምንነትና አስፈላጊነት 24
የስራ አካባቢ ደህንነት የሥራ አመራር ሥርዓት 30
ዓለም አቀፍ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መረጃ (እ.ኤ.አ.2025) 32
“ሴቶች እና የኤች አይ ቪኤድስ” 36
ልዩ ልዩ 38




# የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈጻሚ መልዕክት

በኢትዮጵያ ውስጥ እየተመዘገበ ያለው ሁለንተናዊ ዕድገት ዘላቂ እንዲሆን ለማድረግ አስተማማኝ የኃይል አቅርቦትና ስርጭት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ለሀገራችን ሁለንተናዊ ልማት ወሳኝ የሆነውን የኃይል አቅርቦት አስተማማኝና ተደራሽ ለማድረግ በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

የኃይል አቅርቦቱን ተደራሽ ለማድረግ ከሚከናወነው ሥራ ባሻገር የሠራተኞችን ደህንነት በማረጋገጥ፣ ሠራተኛው ተገቢውን አገልግሎት ለደንበኛው በብቃት እና በጥራት መስጠት እንዲችል በሁሉም የተቋሙ የልማት ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ውስጥ ኤች.አይ.ቪን መከላከል አንዱና ዋነኛው አካል ተደርጎ እየተተገበረ ይገኛል፡፡

ባለፉት አራት አስርት አመታት ኤች.አይ.ቪ. በርካታ ወገኖችን ለከፍተኛ ጉዳት በማጋለጥ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብና በሀገር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡ በተለይ በልማት ተቋማት ላይ አምራችና ገንቢ የሆነውን የህብረተሰብ ክፍል በማጥቃት በድርጅቶች ምርትና ምርታማነት ላይ ጉዳት ሲያደርስ ቆይቷል፡፡

የኤች አይቪ/ ኤድስን ስርጭት አስቀድሞ መከላከል በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፍ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ሰፊ ጉዳት በተሻለ ሁኔታ ለመግታት ያስችላል፡፡ በሽታው በተለይ አምራች የሆነውን የሰው ኃይል በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚያጠቃ የልማት ድርጅቶች የሰው ኃይላቸውን ከኤች. አይ.ቪ. ቫይረስ አሉታዊ ተፅዕኖ ነፃ ለማድረግ የበሽታውን የመከላከል ስራን እንደ ድርጅቱ መደበኛ ስራ ትኩረት ሰጥተው ሲተገብሩ ቆይተዋል፡፡

በዚህ ረገድ ተቋማችን የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ቢሮን በማደራጀትና ወደ ስራ በማስገባት ቫይረሱ በሠራተኛው ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስቀድሞ የመከላከል እንዲሁም በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ጉዳት ለደረሰባቸው ሠራተኞችና የሠራተኞች ቤተሰቦች ድጋፍ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

በተቋማችን ባለፉት ጊዜያት ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ጋር በተያያዘ የተሰራው ስራ አበረታች ቢሆንም ከዚህ የበለጠ ውጤት ለማምጣት ቁርጠኛ መሆናችንን እያረጋገጥሁ፣ ሰራተኛው ራሱንና ህብረተሰቡን ከኤች. አይ.ቪ ቫይረስ በመከላከል ብቁና ጤናማ አምራች ለመሆን የበኩሉን አስተዋፅኦ በማበርከት ኃላፊነቱን እንዲወጣ ለማሳሰብ እወዳለሁ አመሰግናለሁ፡፡

ኢ/ር ጌቱ ገረመው

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈፃሚ



# የመሰረታዊ ሰራተኛ ማህበር ሊቀመንበር መልዕክት

በአንድ ድርጅት ቀጣይነት ያለው ለውጥና ስኬታማ የዕድገት ጉዞ እንዲኖር እውቀት፣ ልምድ እና ብቃት ያለው የሰው ሃይል መኖር ቁልፉ ሚና ይጫወታል፡፡ ሠራተኛው የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የጤንነቱን ሁኔታ የሚጎዱ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመሳሰሉ በሽታዎች እንዳይጋለጥ በግልጽ መመካከርና ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ኤች አይ ቪ/ኤድስ በሰራተኛው፣በቤተሰብ ብሎም በማህበረሰብ የሚያደርሰውን ከፍተኛ ጉዳት ለመቀነስ በተቋማችን ጭምር በተሰሩ ዘርፈ ብዙ ስራዎች መልካም ውጤት የተመዘገበ ቢሆንም አሁን ላይ በወጣቶች ላይ ከፍ ብሎ የሚታየው የቫይረስ ስርጭት ምጣኔ ወረርሽኝ ሆኖ እንዳይነሳ ተጋላጭ የሆኑ የሰራተኛ ክፍሎችን ታሳቢ ያደረገ ሰፊ ትምህርታዊ የቅስቀሳ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል፡፡

የተቋሙ መሠረታዊ ሰራተኛ ማህበር የሰራተኛውን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበርና በመደጋገፍ ለጋራ ውጤትና ዕድገት በትብብር እየሠራ ይገኛል፡ ፡

ማህበሩ የሠራተኛው መብትና ነፃነት ተጠብቆ የተጣለበትን ኃላፊነት በተገቢው መልኩ እንዲወጣ ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ በመሆኑ ሰራተኛውም ያለውን ልምድ፣ ዕውቀትና ክህሎት ተጠቅሞ ከመንግስትና ከህዝብ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት በጥሩ ስነ-ምግባር፣ በቅንነትና በታማኝነት እንዲሁም በትጋትና በተነሳሽነት ስሜት መስራት ይኖርበታል፡፡

በመጨረሻም የመሠረታዊ የሠራተኛ ማህበር የሠራተኛውን የስራ ላይ ደህንነት እና ጤና ለማሻሻል ትኩረት ሰጥቶ ለመስራት ምንጊዜም ዝግጁ መሆኑን እያረጋገጥኩ፤መላው ሠራተኛ ራሱን፣ ቤተሰቡን እና ባልደረባውን ከኤች.አይ.ቪ ስርጭት ለመጠበቅ በንቃት እንዲሳተፍ እና ለሀገራችን እድገትና ብልጽግና የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት አሳስባለሁ፡፡

ሀይሉ ዘውዱ

የመሰረታዊ ሰራተኛ ማህበር ሊቀመንበር




# የሰው ሀብት ልማት ሥራ አስፈጻሚ መልዕክት

የሰለጠነ፣ ልምድና ብቃት ያለው የሰው ሀብት አንድ ተቋም ውጤታማ እንዲሆንና ቀጣይነት ያለው ዕድገት እንዲያስመዘግብ ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረክታል። ብቁና ጤናማ የሰው ኃይል ያላቸው ተቋማት ዘላቂነት ያለው ተከታታይ እድገትና ለውጥ እያስመዘገቡ ለተገልጋዮችም በጥራትና በቅልጥፍና አገልግሎት በማድረስ በኩል ተጠቃሽ መሆን ይችላሉ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በሀገራችን ከሚገኙ ግዙፍ የመንግስት ተቋማት መካከል ከፍተኛ የሰው ሀብት ካላቸው አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚመደብ ነው፡ ፡ ተቋሙ ያሉት ሠራተኞች ከሥራ ላይ አደጋና ኤች.አይ.ቪን ከመሳሰሉት ስጋቶች ነፃ ሆነው ዘመኑ የሚጠይቀውን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት አጣምረው ለተቋሙ ሁለንተናዊ ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት እንዲችሉ የማብቃት ሥራ እየተሠራ ነው።

በተለይ የተቋሙን የሰው ሀብት ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጉዳት ለመከላከል እየተከናወነ ያለው ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫና ትምህርታዊ ስራዎች እንዲሁም የድጋፍና እንክብካቤ ተግባራት ተጠቃሽ ናቸው።

ለበርካታ አመታት በተከናወኑ ስራዎች የተገኘው ውጤት አበረታች ቢሆንም በተቋማችን ያለው ሰራተኛ ስለ ቫይረሱ ያለው ግንዛቤ በተሻለ ሁኔታ እንዲጨምር እና ከራሱ አልፎ ሌሎችን ለማስተማርና ለማንቃት እንዲበቃ ብሎም ኤች.አይ.ቪን በመከላከል ረገድ የመሪነት አስተዋጽኦን እንዲያበረክት አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

መላው የተቋሙ አመራርና ሰራተኞችም ባላችሁ ዕውቀት፣ ልምድና አቅም ሁሉ ተጠቅማችሁ የኤች አይ.ቪ/ ኤድስ ስርጭትና ጉዳት እንዲቀንስ እና በዘርፉ የተሻለ ውጤት እንዲመዘገብ የበኩላችሁን አስተዋጽኦ እንድታበረክቱና ኃላፊነታችሁን እንድትወጡ አሳስባለሁ።

ወ/ሮ ዘሪቱ ፍቅሬ

የሰው ሀብት ሥራ አስፈጻሚ

ተግዳሮቶችን በመቋቋም፣የኤችአይቪ/ኤድስ
ምላሽን ዘላቂነት  እናረጋግጥ!



(Overcoming disruption,
transforming the AIDS response !)




## ተግዳሮቶችን በመቋቋም፣የኤችአይቪ/ ኤድስ ምላሽን ዘላቂነት እናረጋግጥ!

# የ2018 ዓ.ም የዓለም ኤድስ ቀን መሪ ቃል

## የመሪ ቃሉ ፅንሰ ሃሳብ

የዘንድሮው የአለም የኤድስ ቀን! ተግዳሮቶችን በመቋቋም፣የኤችአይቪ/ኤድስ ምላሽን ዘላቂነት እናረጋግጥ! (Overcoming disruption, transforming the AIDS response !) በሚል መሪ ቃል በሀገር አቀፍ ደረጃ ህዳር 22 ቀን 2018 ዓ.ም ታስቦ የሚውል ይሆናል፡፡

የኤች አይ ቪ/ኤድስ ምላሽ አለም አቀፍ ድጋፍ በመቀነሱ ምክንያት ያጋጠመውን የፕሮግራም ዘላቂነት ተግዳሮት ለመቋቋም/ መፍትሄ ለማስቀመጥና አሁን ካለው የኤች አይ ቪ ስርጭትና ተጽዕኖ አንጻር በማየት አጠቃላይ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ምላሹን በተቻለ ፍጥነትና በተነጻጻሪ በዝቅተኛ ኢንቨስትመንት በሽታውን መቆጣጠር በሚያስችል መልኩ እምርታዊ ለውጥ በጋራ ለማምጣት ሚያስችል ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ቃል የሚገባበት ቀን ነው፡፡

የዘንድሮው የአለም ኤድስ ቀን መሪ ቃል ፅንሰ-ሃሳብ በአሁኑ ወቅት ከአለም አቀፍ ድጋፍ ሰጪ አካላት ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ምላሽ ማስፈጸሚያ ሲደረግ የነበረው የገንዘብ ድጋፍ በመቀነሱ ምክንያት የታቀዱ አገራዊ እቅዶችን በታቀደው ልክ ለመተግበር አለመቻል እንዲሁም አጠቃላይ የኤች አይ ቪ/ኤደስ ምላሹ ላይ የተፈጠረውን ከፍተኛ የሆነ የፕሮግራም ዘላቂነት ተግዳሮትን መረዳትና በእቅድና በተደራጀ መልኩ መፍታት አንዱና ዋናው የወቅቱ አጀንዳችን መሆኑን ለማስገንዘብና ለመፍትሄውም በጋራ መረባረብን ያለመ ነው፡፡ የገጠመንን ተግዳሮት በመፍታት ሂደት ውስጥ አብሮ መታየት የሚገባው የኤች አይቪ/ኤድስ ምላሽ ላይ እምርታዊ ለውጥ ማምጣት የሚለው ነው፡፡

## (Overcoming disruption, transforming the AIDS response !)

የፕሮግራሙን ዘላቂነት በማረጋገጥ ሂደት ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው በሽታውን በአጠረ ጊዜ ውስጥና በተነጻጻር ዝቅተኛ በሆነ ኢንቨስትመንት መቆጣጠር አንዱና ዋናው ነው፡፡ ስለሆነም የኤች አይ ቪ/ኤድስ ምላሽ ዘላቂነትን እናረጋግጥ ስንል የምናከናውናቸው የኤች አይ ቪ ፕሮግራሞች ላይ በሽታውን ለመቆጣጠር በሚኖራቸው ፋይዳና ወቅታዊ የበሽታው ሁኔታ አንጻር በማየት ስር-ነቀል ለውጥ ማምጣት አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ዓመት የአለም ኤድስ ቀን መሪ ቃል ተግዳሮቶችን በመቋቋም፣ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ምላሽን ዘላቂነት እናረጋግጥ!' የሚል ሲሆን በአሁኑ ወቅት ያጋጠመው የድጋፍ መቀነስና የኤች አይ ቪ/ኤድስ ምላሽ ዘላቂነት ተግዳሮትን በልዩ ትኩረት መፍታትና የኤች አይ ቪ/ኤደስ አገራዊ ምላሽ ላይ እምርታዊ ለውጥ ማምጣት ጋር በተመጋገበ መልኩ በመፈጸም በሽታውን በተሳካ ሁኔታ መቆጣጠርን ዓላማ ያደረገ ወቅታዊ መሪ ቃል ነው፡ ፡

# በተቋሙ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ቢሮ የተከናወኑ አንኳር ተግባራት

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ኤች አይ ቪ /ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ቢሮ በ2017 በጀት አመት በ12 ወር ውስጥ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከል ሥራዎችን ባልተማከለ መልኩ በሁሉም የተቋሙሪጅን ጽ/ቤቶችና በሌሎችም የሥራ ክፍሎች ውስጥ ለመሥራት በታቀደው መሰረት በርካታ አንኳር ተግባራት ማከናወን የቻለ ሲሆን ዝርዝር አፈጻጸሙም ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡





## ዋና ዋና የትኩረት መስኮች

- የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከል ሥራን ውጤታማነት ማሳደግ እና የኤድስ ፈንድ የድጋፍና እንክብካቤ ሥራዎችን መሥራት፡፡
- ለተቋሙ ሠራተኞች የኤችአይቪ/ኤድስ የመረጃና የማንቂያ ትምህርታዊ ጽሁፍ ማዘጋጀትና እንዲደርሳቸው ማድረግ
- የበሽታውን ስርጭት ለመከላከል የኮንዶም ግዢ እና ሥርጭት ማከናወን
- ከልዩ ልዩ የክልል ቢሮዎች ለተመረጡ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች የኤችአይቪ/ኤድስ የሜይኒስትሪሚንግና የአቻ ለአቻ ሥልጠና መስጠት
- በልዩ ልዩ የክልል ቢሮዎች የሚከናወኑ የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከል ሥራዎችን አፈጻጸም በተመለከተ ክትትልና ምዘና ማድረግ
- በክልል ቢሮዎች ውስጥ የሚገኙ ሠራተኞችን በኤችአይቪ/ኤድስ የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ በቅስቀሳ እና በትምህርት ሥራዎች መድረስ
- ሠራተኞች የኤችአይቪ የደም ምርመራ አድርገው ውጤታቸውን እንዲያውቁና ቀጣይ ህይወታቸውን በእቅድ እንዲመሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ናቸው፡፡



## የተከናወኑ አንኳር ተግባራት

- በተቋሙ ውስጥ ለሚገኙ ለ170 የኤድስ ፈንድ የድጋፍ ተጠቃሚዎች ዘላቂ ድጋፍ እንዲያገኙ አስፈላጊውን ምቹ ሁኔታ የመፍጠር እና ድጋፍ የማድረግ ሥራውንም ከሪጅን ቢሮ አስተዳደር ኃላፊዎች ጋር በቅንጅት በመስራት ማስፈጸም ተችሏል፡፡
- የኤችአይቪ/ኤድስን ስርጭት ለመከላከል የሚያስችል የኮንዶም እና የኤችአይቪ/ኤድስ ወቅታዊ መረጃ የያዙ ጽሁፎች ስርጭት በክልል ቢሮዎች ውስጥ ተከናውኗል፡፡
- ወላጆቻቸው በተቋሙ ይሰሩ የነበሩና በኤችአይቪ/ኤድስ ሳቢያ ያጡ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሳያቋርጡ መቀጠል እንዲችሉ በዓመት አንድ ጊዜ የትምህርት ቤት ዩኒፎርም ከጫማ ጋር ወጪ እንደሚሸፈንላቸው እና ለአመቱ የትምህርት ጊዜ የሚበቃ መሰረታዊ የሆኑ የትምህርት መሳሪያዎች ማሟያ ለእያንዳንዳቸው እስከ ብር 2,500.00 እንደሚሸፈንላቸው በተገለጸው መሰረት ለ2017 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን ለት/ቤት ዩኒፎርምና ጫማ እንዲሁም ለአመቱ የትምህርት ጊዜ የሚበቃ መሰረታዊ የሆኑ የትምህርት መሳሪያዎች ማሟያ ለእያንዳንዳቸው የሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር ድጋፍ እንዲሰጥ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡
- አመታዊ የአለም ኤድስ ቀን እና የነጭ ሪቫንን ቀንን አስመልክቶ በተቋሙ በተዘጋጀው ፕሮግራም በዋናው መስሪያ ቤት እና በአዲስ አበባ ክልል የሚገኙ ሠራተኞችን ያሳተፈ የኤችአይቪ/ኤድስ የግንዛቤ ማስጨበጫና የቅስቀሳ ስራዎችን ለመስራት በታቀደው መሰረት ታህሳስ 3 ቀን 2017ዓ.ም. በዋና መስሪያ ቤት ደረጃ በአዲስ አበባ ክልል የሚሰሩ 200 የሚሆኑ የተቋሙ ሠራተኞች የሚሳተፉበት ፕሮግራም ተዘጋጅቶ በጤናው ዘርፍ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ተጋባዥ መምህራን (በፕሮፌሰር መስፍን አርአያ) እና በሌሎች ባለሙያዎች አማካኝነት ትምህርት፣ ወቅታዊ መረጃና መልእክት የማስተላለፍ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡
- የአለም ኤድስ ቀንን አስመልክቶ በተቋሙ በሁሉም ዋና ዋና የክልል ቢሮዎች ውስጥ የኤችአይቪ/ኤድስ የግንዛቤ ማስጨበጫና የቅስቀሳ ሥራዎችን ለመስራት በታቀደው መሰረት በዋናው መ/ቤት፣ በድሬዳዋ ሪጅን፣ በሀረር ሪጅን፣ በጅግጅጋ ሪጅን፣ በጭሮ ሪጅን፣ በደሴ ሪጅን፣ በደቡብ አዲስ አበባ ሪጅን፣ በምስራቅ አዲስ አበባ ሪጅን፣ በምእራብ አዲስ አበባ ሪጅን፣ በመቀሌ ሪጅን፣ በሽሬ ሪጅን፣ በአምቦ ሪጅን፣ በነቀምት ሪጅን፣ በመቱ ሪጅን፣ በጋምቤላ ሪጅን፣ በቦንጋ ሪጅን፣ በባሌ ሮቤ ሪጅን፣ በሻሸመኔ ሪጅን፣ ወላይታ ሶዶ ሪጅን፣ በአሶሳ ሪጅን፣ አዳማ ሪጅን፣ ጅማ ሪጅን ውስጥ የሚሰሩ በርካታ ሠራተኞች የተሳተፉበት ትምህርታዊ የቅስቀሳ ሥራ ተከናውኗል፡፡
- በተቋሙ የሚከናወኑ የግንዛቤ ማስጨበጫና የቅስቀሳ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዲችሉ ከ32 የክልል ቢሮዎች ለተመረጡ ሠራተኞች ሥልጠና ለመስጠት በታቀደው መሰረት በደብረዘይት ሥራ አመራር ተቋም፣ በአዳማ ከተማ፣ በጅማ ከተማ እና በደሴ ከተማ በአራት ዙር ለ235 የተቋሙ ሠራተኞች የኤችአይቪ መከላከል የአቻ ለአቻ አወያዮች እና የአመራር ክህሎት ላይ ያተኮረ የሶስት ቀን ሥልጠና በዘርፉ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች አማካኝነት ተሰጥቷል፡፡
- ከትምህርታዊ እና የቅስቀሳ ሥራዎች ጋር በጥምረት ሠራተኞች የኤችአይቪ የደም ምርመራ አድርገው ውጤታቸውን እንዲያውቁና ቀጣይ ህይወታቸውን በእቅድ እንዲመሩ ለማድረግ የሚያስችል የኤችአይቪ ምርመራን በማመቻቸት 1,121 ሠራተኞች ምርመራውን አድርገው ውጤታቸውን እንዲያውቁ የማድረግ ሥራ ተከናውኗል፡፡
- የኤችአይቪ/ኤድስ አጠቃላይ መረጃና ትምህርታዊ ጽሁፍ የያዘ የተቋሙ ሠራተኞች የተሳተፉበት ልዩ መጽሄት እና ከ10,000 በላይ በራሪ ጽሁፎች /ብሮሽሮች/ ተዘጋጅተው ለሠራተኞች እንዲሰራጩ በማድረግ ወቅታዊ መረጃ የማድረስ እና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተሰርቷል፡፡
- ከክልል ቢሮዎች ውስጥ በስራ ቦታ ላይ በኤችአይቪ መከላከል ሥራ ላይ መልካም አፈጻጸም ላስመዘገቡ የሥራ ክፍሎች እውቅና ተሰጥቷል፡፡

## በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች

- በተወሰኑ የክልል ቢሮዎች የሚገኙ የኤችአይቪ መከላከል ሥራ አስተባባሪዎች የሥራ ክፍል መቀየር፣
- አዲስ የሚመደቡትም በሥራ ቦታ የሚያከናውኑት የኤች አይ ቪ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርታዊ ሥራዎች ከአለማወቅ የተነሳ በአፈጻጸም ላይ ክፍተት መታየቱ
- እንዲሁም ትምህርታዊ ጽሁፎችንና ኮንዶም የመሳሰሉትን ከማዕከል በወቅቱ ወስዶ ለማሰራጨት አለመቻል፡፡



## የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- ከክልል የሥራ ኃላፊዎች እና የኤችአይቪ መከላከል ሥራ አስተባባሪዎች ጋር ተቀናጅቶ በመስራት ሥራውን ታች ድረስ ለማውረድና በርካታ ሠራተኞችን ተደራሽ ለማድረግ እንዲቻል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር እና ተጨማሪ ቅስቀሳ ሥራ በመስራት ክፍተቱን ለማጥበብ ጥረት ማድረግ
- የኤችአይቪ ኤድስ መከላከል ሥራ ከሚሰሩ አጋር ተቋማትና ባለሙያዎች ጋር በጥምረትና በቅንጅት ለመስራት ጥረት መደረጉ



# ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና አሁናዊ ሁኔታው በዓለም፣በአፍሪካና በሀገራችን

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቫይረስ ስርጭት በዓለም አቀፍ ደረጃ አሁንም ድረስ የቀጠለ ሲሆን እ.ኤ.አ በ2023 ከ40 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ እና ከእነዚህ መካከል ደግሞ ከግማሽ በላይ አፍሪካ ውስጥ እንደሚገኙ የአለም የጤና ድርጅት (WHO) አሳውቋል።

እ.ኤ.አ በ2024 በዓለም አቀፍ ደረጃ 40.8 ሚሊዮን (39.4 ሚሊዮን አዋቂዎችና 1.4 ሚሊዮን 0-14 እድሜ) ሰዎች ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው እንደሚገኝ፣ 630 ሺህ በላይ ሰዎች ሕይወታቸውን በኤድስ ምክንያት ያጡ መሆናቸውንና በዚሁ ዓመት 1.3 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች አዲስ በኤች.አይ.ቪ. የተያዙ መሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በአለም አቀፍ ደረጃ ከመከላከል እና ከመቆጣጠር አንፃር አዲስ በኤች.አይ. ቪ. የመያዝ ምጣኔ ከፍተኛ ከነበረበት እ.ኤ.አ ከ2010 ጋር ሲነፃፀር 40 በመቶ መቀነሱ እና በኤድስ ምክንያት የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር ከፍተኛ ከነበረበት እ.ኤ.አ ከ2010 ጋር ሲነፃፃር 54 በመቶ መቀነሱን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እ.ኤ.አ በታህሳስ 2024 31.6 ሚሊዮን ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው የሚገኝ ማህበረሰብ ፀረ ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት እየወሰዱ እንደነበር የዩኤን ኤድስ መረጃ ያመለክታል፡፡

በአፍሪካ 25.6 ሚሊዮን ሰዎች ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው እንደሚገኝ ይገመታል። ከነዚህ ውስጥ 90 በመቶ የሚሆኑት ተመርምረው ኤች አይ ቪ. በደማቸው እንደሚገኝ ያወቁ፣ 82 በመቶ የሚሆኑት የፀረ ኤች አይ ቪ. መድሃኒት እየወሰዱ ያሉ፣እንዲሁም 76 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ የቫይረስ መጠን ምርመራ ውጤታቸው ከ1000 ኮፒ በታች መውረዱን መረጃዎች ያሳያሉ። እ.ኤ.አ በ2023 ከሰሃራ በታች ባሉ ሀገራት አዲስ በኤች. አይ. ቪ




ከሚያዙ መካከል 62 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው።


የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እ.ኤ.አ በ2024/2025 ባካሄደው ጥናታዊ ትንበያ መሰረት በሀገራችን እድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የኤች.አይ.ቪ. የስርጭት ምጣኔ 0.67% (ከፍተኛው ጋምቤላ 3.1% እና ዝቅተኛው ሶማሌ 0.2%) ሲሆን በዚህም ስሌት 601 ሺህ 39 በላይ የሚሆኑ ወገኖች ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው እንደሚገኝ፣ 7 ሺህ 962 ሰዎች በዓመቱ ውስጥ አዲስ በኤች.አይ.ቪ. እንደሚያዙ እንዲሁም 9 ሺህ 560 ሰዎች ደግሞ በኤድስ ምክንያት እንደሚሞቱ ያመላክታል፡፡

እ.ኤ.አ በ2024/2025 የተገመተው አጠቃላይ አዲስ በኤች.አይ.ቪ. የሚያዙ ሰዎች ብዛት 7 ሺህ 962 ነው። ከእነዚህም ውስጥ ከ0 -14 ዓመት መካከል ያሉ ህፃናት 1 ሺህ 235 (16%)፣ ከ15-24 ዓመት ያሉ ወጣቶች 2 ሺህ 682 (34%) እና 25 ዓመት እና ከዚያ በላይ ዕድሜ ያላቸው አዋቂዎች ደግሞ 4 ሺህ 45 (51%) ድርሻ ይይዛሉ፡፡

ከ10-19 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ደግሞ 1 ሺህ 147 ያህል ድርሻ እንዳላቸው ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ ከተገመተው አገራዊ አዲስ የሚያዙ ሰዎች ብዛት ማለትም 7 ሺህ 962 ውስጥ ኦሮሚያ (4 ሺህ 138)፣ አማራ (1 ሺህ 124)፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ (534)፣ ደቡብ ኢትዮጵያ (456) እና መካከለኛ ኢትዮጵያ (446) ድርሻ እንዳላቸው ያሳያል፡፡

እነዚህ ክልሎች በአጠቃላይ ከተገመተው አገራዊ አዲስ በኤች.አይ. ቪ. የመያዝ ምጣኔ ላይ ወደ 84% ያህል አዲስ በኤች.አይ.ቪ. የመያዝ ምጣኔን ይወስዳሉ። ከ15-24 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ወጣቶች መካከል ከፍተኛ የሆነ አዲስ በኤች አይ ቪ. የመያዝ ምጣኔ የተመዘገቡባቸው ክልሎችን ስናይ ደግሞ ኦሮሚያ (3 ሺህ 545)፣ አማራ (747)፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ (465) እና መካከለኛ ኢትዮጵያ (392) እንደሆኑ ያሳያል።

ከ10-19 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ደግሞ 1 ሺህ 147 ያህል ድርሻ እንዳላቸው ያሳያል





በክልልም ውስጥ ከቦታ ቦታና፣ በከተማ (2.9%) እና በገጠር (0.4%) እንዲሁም በማህበረሰብ ክፍሎች የስርጭት ምጣኔ የሚለያይ ሲሆን በቅርቡ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የIBBS 2024 የተደረገ ጥናት ይበልጥ ተጋላጭ የአፍላ ወጣትና ሴቶች የኤች.አይ.ቪ. የስርጭት ምጣኔ 1.7% እንደሆነ አሳይቷል።

የኤች.አይ.ቪ. ስርጭት ከፍተኛ ከነበረበት አሁን ወዳለበት 0.67% ለመቀነስ ማህበረሰቡ ያበረከተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ በየጊዜው የስርጭቱን ሁኔታ ታሳቢ ያደረጉ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል አካታች የሆነ የኤች.አይ.ቪ. መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎቶች በስፋት በመተግበራቸው ነው፡፡

በ2030 ኤድስ የማህበረሰቡ የጤና ችግር ወደ ማይሆንበት ደረጃ ማድረስ የሚለውን አለም አቀፍ ራዕይ ከግብ ለማድረስ አገራት ስምምነት ተቀብለው በመተግበር ላይ ይገኛሉ፡፡ አገራችንም ይህንን ራዕይ ከግብ ለማድረስ የተለያዩ ግቦችን አስቀምጣ በመተግበር ላይ ትገኛለች፡፡ የተቀመጡ ግቦችም እ.ኤ.አ በ2025 ሶስቱን 95 ማሳካት ነው፡፡

ይህም ማለት ኤች አይ ቪ በደማቸው ከሚገኝ ሰዎች ውስጥ 95% የሚሆኑትን ተመርምረው ራሳቸውን እንዲያውቁ ማድረግ፤ ተመርምረው ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው መገኘቱን ካወቁት ሰዎች ውስጥ 95% የጸረ-ኤች.አይ.ቪ. ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ፤ ህክምና ከጀመሩት ሰዎች ውስጥ ደግሞ 95% ህክምናቸውን በትክክል ተከታትለው በደማቸው ውስጥ ያለውን የቫይረስ መጠን በሚጠበቀው ልክ ዝቅ እንዲል ማድረግ ነው፡፡

በተጨማሪም ኤች.አይ.ቪ. ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ መግታት ወይም ከ5% በታች ማድረስ የሚል ግብ የተቀመጠ በመሆኑ አገራችንም ይህን ግብ ለማሳካት በትግበራ ላይ ትገኛለች፡፡

ኤች.አይ.ቪ. በ1992 ዓ.ም ከነበረበት 3.3% ከፍተኛ የስርጭት መጠን አሁን ወዳለበት 0.87% እንዲቀንስ ከፍተኛ ስራዎች ተሰርተዋል። ይሁን እንጂ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት ምጣኔ በፊት ከነበረው ምጣኔ ጋር ሲነፃፀር የቀነሰ ቢሆንም በ2030 ምጣኔውን ዜሮ ለማድረስ ከተቀመጠው ግብ አንፃር በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታየው ከፍተኛ ምጣኔ አሁንም በርካታ ስራዎች መሠራት እንዳለባቸው የሚያመላክት ነው።

ምንጭ፡- (UNAIDS GLOBAL AIDS UPDATE፣WMCC (UNAID Factsheet እና የኢትዮጵያ ጤና ኢንስቲትዩት፣








# የኤች.አይ.ቪ ኤዲስ መተላለፊያ መንገዶች

የኤች አይ ቪ ቫይረስ ከሰውነት ከወጣ በኋላ በጣም ደካማ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ አይቆይም ወድያውኑ ይሞታል። በዛ የተነሳ ነው ኤች አይ ቪ ከማንም ሰው ጋር በምናደርጋቸው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ማለትም በእጅ መጨባበጥ፣መተቃቀፍ እና መሳሳም ሊተላልፉ እንደማይችሉ እና በተጨማሪም ኤች.አይ.ቪ. በመጸዳጃ ቤት መቀመጫ፣ በበር መከፈቻ፣ በብርጭቆ መጠጫ፣በምግብ ወይም በማንኛውም አይነት እንስሳ እንደ ቢንቢ ንክሻ በመሳሰሉት ሊይዝ አይችልም።

ኤች.አይ.ቪ. ለመያዝም ሆነ ለማስተላለፍ የሚችሉበት መንገዶች የተለያዩ ናቸው፣መተላለፊ መንገዶቹ ምን እንደሆኑ ማወቁ በጣም ጠቃሚ ነው። ስለ ኤች አይ ቪ ዕውቀት ያለውን ሰው ማነጋገር ተገቢ ሆኖ ሳለ ይህንንም ከታች የተዘረዘረውን በተግባር ላይ ቢያውሉት መልካም ነው፣

## ኤች አይ ቪ በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊተላለፍ ይችላል

የኤች.አይ.ቪ. ኤዲስ ቫይረስ በሚከተሉት መተላለፊያ መንገዶች ሊተላለፍ ይችላል፤ከዚህም መካከል ቫይረሱ ያለበት ሰው የተጠቀመበትን መርፌ ሌላ ሰው ሲጠቀምበት፣ቫይረሱ ካለበት ሰው ጋር በሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ በኤች አይ ቪ የተለከፈች እናት ከመውለድዋ በፊት ወይም በወሊድ ጊዜ ወይም በምታጠባበት ጊዜ ወደ ልጅዋ ሊተላለፍ ይችላል።

## የኤች አይ ቪ/ኤድስ ዋና ዋና መከላከያ መንገዶች

በአገራችን ዋነኛው የኤች.አይ.ቪ. መተላለፊያ መንገድ ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነት ነው፡፡ ስለዚህ ይህን በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፈውን ኤች.አይ.ቪ. ለከመላከል የ"መ"ህጎች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የ"መ"ህጎች የሚባሉት ደግሞ መታቀብ፣መወሰን፣መጠቀም፣ መመርመር እና መታከም ናቸው፡፡

የመጀመሪያው የ"መ"ህግ መታቀብ ሲሆን ይህም ከጋብቻ በፊት ከሚደረግ የግብረ ስጋ ግንኙነት መታቀብ ወይም የወሲብ ግንኙነት ከመፈፀም ሙሉ በሙሉ መቆጠብ (Abstinence) ማለት ነው፡፡ሁለተኛው የ"መ" ህግ ደግሞ መወሰን ነው ይህም ማለት አንድ ለአንድ መወሰን (ለፍቅረኛ/ ለትዳር/ አጋር ታማኝ መሆንን ያመላክታል፡፡

ሶስተኛው የ"መ"ህግ መታቀብና መወሰን ላልቻለ መጠቀም ኮንዶምን ሁልጊዜ እና በአግባቡ በመጠቀም ቫይረሱን መከላከል እንዲችል የሚያስገነዝብ ነው፡፡

አራተኛው የ"መ"ህግ መመርመር ሲሆን ማንኛውም አካል የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎቶች ተጠቃሚ በመሆን ኤች አይ ቪን መከላከል እንደሚችል ያመላክታል፡፡ መመርመር የኤች.አይ.ቪ. ወደ ሌሎች ሰዎች እንዳይተላለፍ ጥንቃቄ ለማድረግ እና ከእናት ወደ ልጅ የሚተላለፈውን ኤች.አይ.ቪ. ኤዲስ ስርጭት ለመከላከል ይረዳል፡፡

የመጨረሻው የ"መ"ህግ መታከም ነው፤ይህ በደሙ ውስጥ የኤች አይ ቪ ቫይረስ የተገኘ ማንኛውም ሰው የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሀኒት በአግባቡ መውሰድ የቫይረሱን መጠን ለመቀነስ፣ በሰውነት ውስጥ የሚገኝ የመከላከል አቅምን ለመጨመር፣ተጓዳኝ በሽታዎችን ለመከላከል እና ከቫይረሱ ጋር ተስማምቶ እንደ ማንኛውም ጤናማ ሰው ለመኖር ይረዳል፡፡



# የሥራ ላይ ደህንነት ምንነትና አስፈላጊነት



በዓለም ጤና ድርጅት ትርጓሜ መሰረት ጤንነት ማለት የበሽታ አለመኖር፣ ከአካል ጉዳት ህመም ነጻ መሆን፣ የአዕምሯዊ፣ አካላዊ እና የስነ-ልቦና ደህንነት ማረጋገጥ ሲሆን ድርጅቱ ስለ የሥራ ላይ ደህንነት በሚሰጠው ትርጓሜ ከሥራ ባህሪ ጋር ተያይዞ ከሚፈጠር በሽታ ነፃ መሆን፣ ለአካል ወይም ለአዕምሯዊ ጉዳት አለመጋለጥ እንዲሁም የአዕምሯዊና የማህበራዊ ደህንነትን ማረጋገጥ ይጨምራል።

በሌላ አገላለፅ በሥራ ከባቢ ሊፈጠሩ ከሚችሉ ኬሚካላዊ፣ ባይሎጂካል፣ ኤሌክትሪክ፣ አካላዊና ከስነ-ልቦናዊ ጉዳቶች የሠራተኞችን ጤንነት መጠበቅና ሁሌም ደህንነታቸውን ማረጋገጥ እንደሆነ ያብራራል።

ለሥራ ላይ ደህንነት አለመኖር በርካታ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱና ዋነኛው በየተቋሙ ደካማ የሥራ ላይ ደኅንነት ባህል መኖር ነው። የሥራ ላይ ደህንነት ባህል ሲባል በአንድ ተቋም ውስጥ ያሉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በሥራቸው ላይ ለደህንነታቸው የሚያደርጉት ጥንቃቄ፣ ስለሥራ ላይ ደህንነት ያላቸው አመለካከት፣ እውቀት፣ ዝንባሌ፣ ባህሪ ወዘተ... ማለት ነው።

በአንድ ተቋም የሚኖር የሥራ ላይ ደህንነት ባህል አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ሊሆን እንደሚችል የሚቀርቡ ሳይንሳዊ ማብራሪያዎች ያሳያሉ። አዎንታዊ የሥራ ላይ ደህንነት ባሕል ያላቸው ድርጅቶች መገለጫቸው ጠንካራ የሥራ ላይ ደህንነት መመሪያና ፖሊሲ ያላቸው፤የተቋሞቹ አስተዳደሮች በእያንዳንዱ ውሳኔያቸው የሥራ ላይ ደህንነትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ውሳኔ የሚወስኑ፤ በሥራ ላይ አደጋ ሲፈጠር አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጡ፤



ተጠያቂነትን የማረጋገጥ እና ሠራተኞች ለሥራ ላይ አደጋ እንዳይጋለጡ የቅድመ-መከላከል ሥራን አስቀድመው የሚሰሩ ናቸው።

በተጨማሪም አዎንታዊ የሥራ ላይ ደህንነት ባህል ሲኖር በተቋሙ ውስጥ ያሉ አብዛኛው ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሥራ ላይ ደህንነት ግንዛቤ ያላቸውና በእያንዳንዱ ሥራቸው ጥንቃቄ የሚያደርጉ ሲሆን ስለ ሥራ ላይ ደህንነት ግድ የማይሰጣቸው ሠራተኞች በእንደዚህ ዓይነት ተቋም ውስጥ ቁጥራቸው አናሳ ነው። በመሆኑም በሠራተኞች ላይ የሚደርስ የአካል ጉዳትና ሞት አነስተኛ ሲሆን ሠራተኞች በተቋሙ ውስጥ ተረጋግቶ የመሥራት ሁኔታ በሰፊው ይታያል።

ከዚህ በተቃራኒ አሉታዊ የሥራ ላይ ደኅንነት ባህል ሲኖር አብዛኞቹ ሠራተኞች ስለ የሥራ ላይ ደህንነት ግንዛቤ አይኖራቸውም፤ የሥራ ላይ ደህንነት የማይጠቅም ወይም የማያስፈልግ ነው ብለው የሚያምኑ ሲሆኑ ስለ የሥራ ላይ ደህንነት ግልፅ አቅጣጫና አመራር ከኃላፊዎቻቸው አይሰጣቸውም፡ ፡ በተጨማሪም የተቋም አስተዳደሮች ውሳኔ ሲሰጡ የሥራ ላይ ደህንነትን ከግምት አያስገቡም። እንደውም የሥራ ላይ ደህንነት ከማስቀደም ይልቅ ጤንነታቸውን ሊጎዳ በሚችል መልኩ ጫና ፈጥሮ የማሠራት ዝንባሌ ይታያል።

## የስራ ላይ አደጋ መንስኤዎች

የስራ ላይ አደጋ በተለያዩ ምክንያቶች አንድ ሠራተኛ ተገቢውን የስራ ላይ ደህንነት ጥንቃቄዎችን ባለመፈፀም የሚከሰት ድንገተኛ አደጋ ሲሆን በሰው ህይወት፣ በአካል፣ በአዕምሮና በንብረት ላይ ድንገተኛ አደጋ ሊያስከትል ይችላል።

የስራ ላይ አደጋዎች መንስኤያቸው የተለያየ ሊሆን ቢችልም 88 በመቶ አደጋዎች ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶችን (Unsafe act) ማለትም በጥንቃቄ ጉድለት፣ በአሠራር ችግር፣ በአደረጃጀት እና ሰው ሰራሽ በሆኑ ችግሮች ምክንያት የሚደርሱ ናቸው።

10 በመቶው ደግሞ ለስራ በምንጠቀምባቸው መሳሪያዎችና (Unsafe conditions) ምቹ ባልሆኑ የስራ ከባቢዎች (poor housekeeping or Environment) ማለትም ንፅህና የጎደለው የስራ አካባቢ፤ የተበላሹ ወይም የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፉ መሳሪያዎችን ለስራ መጠቀም፤ በቂ ብርሃን በሌለበት ቦታ በመሥራት ምክንያት ይከሰታሉ።

ቀሪው 2 በመቶ አደጋ በተፈጥሮ ወይም ከእኛ ቁጥጥር ውጭ በሆነ ምክንያት የሚከሰቱ እንደሆኑ ጥናቶች ያመለክታሉ።





## ሰራተኞች ለአደጋ የሚጋለጡባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች፡-

- ሥራን በአጭር ወይም በአቋራጭ ለመስራት መፈለግ /Short cut system/
- ሥራ በቅደም ተከተሉ መሰረት አለመስራት/ Shortage of procedure/
- ከልክ ያለፈ በራስ መተማመን /Over confidence/
- ስለስራው ሙሉ መረጃ ወይም በቂ እውቀት አለመኖር /Shortage of full information/
- ስለምንሠራው ስራ ጥቂት መረጃ ኖሮን ስንሰራ /incomplete information/
- የምንሰራበትን የስራ አካባቢ በንፅህና አለመያዝ ወይም የተዝረከረከ የስራ ቦታ ላይ ስራ ማከናወን /Poor housekeeping/
- ያልተደራጀ ወይም መልክ የሌለው ስራ በመስራት /an proper arrangement/
- የስራ ላይ ደህንነት መመሪያዎችን፤ ደንቦችንና ህጎችን ችላ በማለት / Ignoring safety/
- ስራው የሚጠይቀውን ስነ-ስርዓት አለማክበር፤ ጠጥቶ መስራት /Un disciplinary/
- የምንሰራውን ስራ ምንነት ሙሉ ለሙሉ አለማወቅ /Shortage of Knowledge/
- ስራን በተረበሸ አዕምሮ ወይም በጤና እክል ላይ እያሉ መስራት /Mental disturbance/

## በስራ ቦታ የሚከሰቱ አደጋዎችና ተፅዕኖቸው

በስራ ቦታ ላይ የሚከሰት አደጋ በሠራተኞች፣ በአሠሪው ድርጅት፣በተጎጂ ቤተሰብ ብሎም በሀገር ላይ ከቀላል እስከ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡

በሥራ ላይ የሚከሰት አደጋ በሰራተኛው ላይ በአደጋው ምክንያት የሚደርስ ስቃይ እና ከአደጋው በኋላ በአዕምሮ ውስጥ የሚቀረፅ ፍርሃትና ጭንቀት / Mental disturbance/፤ የህይወት ዘመን ጉዳት /Permanent disability/፤ ተመሳሳይ ስራ ያለመሥራት አጋጣሚ /Unable to do the same job again/ እና የገቢ ምንጭ መቋረጥ ወይም ማነስ የመሳሰሉት ተፅዕኖዎችን ያመጣል፡፡

የሚፈጠረው አደጋ የተጎጂ ቤተሰብ የቤተሰብን አባል በሞት እንዲነጠቁ ምክንያት ይሆናል፡፡ ለኢኮኖሚ ቀውስ ብሎም ልጆችን ለከፋ ችግር ይዳርጋል፡፡

በተመሳሳይ በአሠሪው ድርጅት ላይ የምርት መቀነስ /Loss of production/፣ተጨማሪ የትርፍ ሰዓት ክፍያ /additional overtime fee/፣ በአደጋ የተጎዱ ማሽኖች የጥገና ወጪ /Maintenance expenses/፣ የስራ ሰዓት ብክነትና የህክምና ወጪ /absenteeism and medical expense increases/፣ የጉዳት ካሳ ክፍያ /increases compensation fee/፣ የተዛባ የኢንዱስትሪ ሰላም /Bad industrial relation/ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

መሠል አደጋዎች በአገር ላይ የሚፈጥሩት ጫናም ቀላል አይደለም፡ ፡ የተማረ ኃይል ማጣት (Loss of skilled manpower) እንዲሁም የኢኮኖሚ ቀውስ እንዲፈጠር ያደርጋል (Increases dependency ratio/.



## የስራ ላይ ደህንነት መመሪያዎች

በሥራ ቦታ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠሩ አደጋዎችን ለመቀነስ የሥራ ኃላፊዎች ለአደጋ የሚዳርግ አሰራርን ማስወገድ፤ ሰራተኞች ለስራው ተስማሚ የሆነ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች ወይም አልባሳት መጠቀማቸውን ማረጋገጥ፤ ለስራው ተስማሚ የሆኑ መሳሪያዎችን ብቻ እንዲጠቀሙ ማድረግ፤ የተቀናጀ እና ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ስራ እንዲሰራ ማድረግ እንዲሁም የሥራ ላይ ደህንነት ደንቦች ሥራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ሠራተኞችም ራሳቸውን በሥራ ላይ ከሚፈጠር አደጋ ለመከላከል የራሳቸውንና የባልደረቦቻቸውን ደህንነት የመጠበቅ፤ የህዝብና የድርጅት ንብረትን ከአደጋ የመጠበቅ፤ የድርጅቱን የሙያ ደህንነት መመሪያዎች፣ ደንቦችና ህጎች የማወቅ እና በስራ ላይ የማዋል፤ የሚሰሩት ሥራ ለአደጋ የሚያጋልጣቸው ሆኖ ሲያገኙት ሁኔታውን ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ እንዲሁም በሥራ ቦታ የደረሰን ማናቸውንም አደጋ (የሰውም ሆነ የንብረት) ለቅርብ ኃላፊያቸው ሪፖርት ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

በተያያዘ በስራ ወቅት ሰራተኛው አደንዛዥ ዕፅ ወይም መጠጥ ጠጥቶ ስራ ቦታ አለመገኘት፤ በስራ ቦታ የማይገባ ቀልድ አለመቀለድ፤ በስራ ላይ ያለን ሰራተኛ ትኩረት የሚስቡ ማናቸውንም ድርጊቶች ከመፈፀም መቆጠብ ይገባል፡፡

## የሥራ ቦታን ንፁህ፣ ለሥራ ተስማሚና ከአደጋ ነፃ ለማድረግ፡-

- ለስራ የምንጠቀምባቸውን መሳሪያዎች በተገቢው ቦታ ማስቀመጥ እና የስራ አካባቢን በየጊዜው ማፅዳት፤
- የመስሪያ መሣሪያዎች አያያዝና አቀማመጥ ለአደጋ ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ መረዳት፤
- በስራ ቦታ ያሉ መተላለፊያ መንገዶችንና ደረጃዎች ከሚያንሸራትቱ ነገሮች የፀዱ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- የስራ ቦታ ወይም አካባቢ በቂ ብርሃን እንዲኖረው ማድረግ፤
- ስለታማ ነገሮችን ከስራ ቦታ ማራቅ፤
- የውሃ እና የኤሌክትሪክ መስመሮች በምንሠራበት አካባቢ አለመኖራቸውን ማረጋገጥ፤
- ተንቀሳቃሽ የመስሪያ መሳሪያዎችን (ግራይንደር፤ድሪል ማሽኖችን) ከተጠቀምንባቸው በኋላ በስርዓት ማስቀመጥ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ የሚደርሰውን ሰብዓዊና ቁሳዊ አደጋዎችን ለመቀነስ ሰራተኛው በስራ ቦታ የሥራ ላይ ደህንነት ደንቦችን አክብሮ መስራት፤ በየደረጃው የሚገኙ የስራ ኃላፊዎችም ሰራተኛው የሥራ ላይ ደህንነቱ እንዲጠበቅ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፤ድርጅቱም የህግና የሞራል ግዴታውን ለመወጣት ወቅታዊ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችን አቅርቦት መፈፀም በስራ ቦታ የሚደርስ ድንገተኛ አደጋን ትርጉም ባለው ሁኔታ በጋራ ለመከላከል ብሎም ለመቀነስ ያስችላል፡፡




Safety
first
WORK
SAFETY
Regulations
Hazards
Protection
Health
Procedures
Danger

# የሥራ አካባቢ ደህንነት አመራር ሥርዓት
# (ISO 45001 Work Place Safety Management System)
# ለምን ያስፈልጋል?

በዓለማችን ማንኛውም ሠራተኛ፣የሥራ መሪም ሆነ ባለሀብት እንዲፈጠር የሚፈልጉት የጋራ ጉዳይ ቢኖር በሥራ አካባቢ የሚከሰት አደጋ እንዲቀንስና የተሻለ የሥራ ቦታ እንዲፈጠር ነው። በመሆኑም ይህንን የጋራ ጉዳይ ለማሳካት የተዘጋጀውን የሥራ አካባቢ ደህንነት አመራር ሥርዓት (ISO 45001 work place safety management system) በመተግበር እንዴት የሥራ ላይ አደጋን መቀነስና የተሻለ የሥራ አካባቢ መፍጠር እንደሚቻል መመልከቱ ተገቢ ነው።

ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በቀን ውስጥ በየ15 ደቂቃው ቢያንስ አንድ ሠራተኛ ከሥራ ጋር በተያያዘ በሚፈጠር አደጋ ወይም በሽታ የሚሞት ሲሆን 153 ሠራተኞች ደግሞ ከሥራ ጋር በተያያዘ በሚፈጠር አደጋ አካል ጉዳተኛ ይሆናሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃም ከሥራ ደህንነት ጋር በተያያዘ በሚፈጠሩ አደጋዎች በዓመት 2.8 ትሪሊየን ዶላር ኪሳራ ይመዘገባል። ይህ ደግሞ በተቋምና በሕብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳድራል።

ይህን ችግር ሊፈታ የሚችል የአመራር ሥርዓት በመዘርጋት የሚፈጠረውን አደጋ ለመቆጣጠር አይነተኛ መፍትሔ በመሆኑ የሥራ አካባቢ ደህንነት አመራር ሥርዓት (ISO 45001 Work Place Safty Management System) መገንባት አስፈላጊ ይሆናል። በመሆኑም ለሁሉም ተቋማትና ኢንዱስትሪዎች የአሠራር ሥርዓቱን መተግበር ለሠራተኞች ምቹ የሆነ የሥራ አካባቢ ከመፍጠሩም ባሻገር በሥራ ቦታ የሚፈጠሩ አደጋዎችን ለመከላከል ያስችላል።

በተጨማሪም በአምራች ወይም በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሥርዓቱ ከተዘረጋ፣ለሠራተኞች መልካም የሥራ አካባቢ እንዲፈጠር መሰረት የሚጥል ሲሆን በሥራ ላይ ለሚፈጠሩ አደጋዎች የሚያወጣውን አላስፈላጊ ወጪ በመቀነስ ምርታማነት እንዲጨምር ይረዳል። ስለዚህ ይህ የአሠራር ሥርዓት በዓለም አቀፉ የንግድ መድረክ ተወዳድሮ ለማሸነፍ እንደ አንድ መሳሪያም የሚያገለግል ስለሆነ የአሰራር ሥርዓቱን መትከል የተቋምን ህልውና አደጋ ውስጥ እንዳይገባ ይከላከላል።

ይህ ደረጃ ከጥራት ሥራ አመራር ሥርዓት (ISO፡9001 Quality Management System) እና ከአካባቢ ደህንነት አመራር ሥርዓት (ISO 14001 Environmental Management Systems) የአሠራር ሥርዓቶች ጋር ተመጋጋቢና ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ያለምንም ችግር ቀላል በሆነ መንገድ ተሳስሮ ሊተገበር የሚችል ሲሆን ደረጃው በሥራ አካባቢ ከሥራ ጋር በተያያዘ የሚደርሱ አደጋዎችን በመለየት የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስና ለማስወገድ የምንጠቀምባቸው ዘዴዎች የሚያመላክት የሥራ አመራር ሥርዓት እንጂ በምርት አጠቃቀምና ጥበቃ ላይ ያተኮረ አይደለም።




ዓለም አቀፍ
የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መረጃ
(እ.ኤ.አ.2025)

- 40.8 ሚሊዮን [37.0 ሚሊዮን –45.6 ሚሊዮን] ሰዎች አሁን ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ይገኛል፡፡
- እ.ኤ.አ. በ2024 ብቻ 1.3 ሚሊዮን [1 ሚሊዮን–1.7 ሚሊዮን] ሰዎች በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ አዲስ በኤችአይቪ ተጠቅተዋል፡፡
- እ.ኤ.አ. በ2024 በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ 630 ሺህ [490 000–820 000] ሰዎች ህይወታቸውን በኤድስ ምክንያት አጥተዋል፡፡
- እ.ኤ.አ. በ2024 31.6 ሚሊዮን [27.8–32.9 ሚሊዮን] ሰዎች የፀረ ኤች.አይ.ቪ. መድኃኒት እየወሰዱ ይገኛሉ፡፡
- 91.4 ሚሊዮን [73.4 ሚሊዮን–116.4 ሚሊዮን] ሰዎች ቫይረሱ ከታወቀ ጊዜ አንስቶ በኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ ተጠቅተዋል፡፡
- 44.1 ሚሊዮን [37.6 ሚሊዮን–53.4 ሚሊዮን] ሰዎች ቫይረሱ ከታወቀ ጊዜ አንስቶ በኤድስ ምክንያት ህይወታቸው አልፏል፡፡

## ኤች.አይ.ቪ በደማቸው የሚገኝ ሰዎች


- በ2024 40.8 ሚሊዮን [37.0 ሚሊዮን –45.6 ሚሊዮን] ሰዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ፡-
  - 39.4 ሚሊዮን [35.7 ሚሊዮን–44.0 ሚሊዮን] ታዳጊዎች፣ ወጣቶችና ጎልማሶች (15 ዓመት በላይ የሆናቸው)
  - 1.4 ሚሊዮን [1.1 ሚሊዮን–1.8 ሚሊዮን] ከ0–14 ዓመት የሆናቸው ህጻናት ናቸው፡፡
  - አጠቃላይ ኤች.አይቪ. በደማቸው ከሚገኝ ሰዎች ውስጥ 53% ሴቶች ናቸው፡፡
- በ2024 87% [69–>98%] ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ከሚገኝ ሰዎች ውስጥ ተመርምረው ውጤታቸውን ያወቁ
- በ2024 5.3 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ምርመራ ባለማድረጋቸው ምክንያት ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው እንደሚገኝ አያውቁም፡፡

## ኤች.አይ.ቪ በደማቸው የሚገኝና የፀረ ኤች.አይ.ቪ መድኃኒት እየወሰዱ የሚገኙ ሰዎች

- እ.ኤ.አ. በ2010 7.7 ሚሊዮን [6.7–8 ሚሊዮን] የሚሆኑ ሰዎች ብቻ የፀረ ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት ይወስዱ የነበረ ሲሆን እ.ኤ.አ. በታህሳስ 2024 መጨረሻ ላይ ግን 34 ሚሊዮን ሰዎች የፀረ ኤች.አይ.ቪ. መድኃኒት እንዲወስዱ የሚጠበቅ ቢሆንም 31.6 ሚሊዮን [27.8–32.9 ሚሊዮን] ሰዎች የፀረ ኤችአይቪ መድሃኒት እየወሰዱ ይገኛሉ፡፡








- እ.ኤ.አ በ2024 ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ ከሚገኝ ወገኖች 77% [62–90%] የሚሆኑት ተገቢ የህክምና አገልግሎት አግኝተዋል፡፡
- እ.ኤ.አ. በ2024 ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ ከሚገኝ እርጉዝ ሴቶች ውስጥ 84% [72 –>98%] የፀረ ኤች.አይ.ቪ. መድኃኒትና ህክምና አግኝተው ቫይረሱ ወደ ህጻኑ እንዳይተላለፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

## አዲስ በኤች.አይ.ቪ የተያዙ

- አዲስ በኤች.አይ.ቪ. የሚያዙ ሰዎች ቁጥር የቫይረሱ ስርጭት ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ከነበረበት እ.ኤ.አ. 1996 አንጻር በ61% ቀንሷል፤
- እ.ኤ.አ. በ2024 1.3 ሚሊዮን [1 ሚሊዮን–1.7 ሚሊዮን] የሚሆኑ ሰዎች በአንድ ዓመት ጊዜ አዲስ በኤች.አይ.ቪ. የተያዙ ሲሆን
  - እ.ኤ.አ. በ2024 በአንድ አመት ጊዜ አዲስ በኤች.አይ.ቪ. ከተያዙ ሰዎች ውስጥ 45% ሴቶችና ልጃገረዶች ናቸው፡፡
  - አዲስ በኤች.አይ.ቪ. ከሚያዙ ሰዎች መካከል የህጻናት ተጠቂዎች ቁጥር የቫይረሱ ስርጭት ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ከነበረበት እ.ኤ.አ. በ2010 አንጻር በ62% ቀንሷል፡፡

### በኤድስ ምክንያት ህይወታቸውን ያጡ

- ህይወታቸውን በኤድስ ምክንያት የሚያጡ ሰዎች ቁጥር ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ከነበረበት እ.ኤ.አ. 2004 አንጻር አሁን ላይ 70% ቀንሷል፡፡
- እ.ኤ.አ. በ2024 በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ 630 ሺህ [490,000–820,000] የሚሆኑ ሰዎች በኤድስ ምክንያት ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡
- እ.ኤ.አ. 2010 በኤድስ ምክንያት ህይወታቸውን የሚያጡ ህጻናትና ታዳጊ ልጆች 240 ሺህ [160,000–340,000] የሚጠጋ የነበረ ሲሆን፣ እ.ኤ.አ. በ2024 75 ሺህ [50,000–110,000] የሚሆኑ ህጻናትና ታዳጊ ልጆች በኤድስ ምክንያት ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡
- በ2024 በዓለም ላይ በእያንዳንዱ ደቂቃ በኤች.አይ.ቪና ተጓዳኝ በሽታዎች ምክንያት የሰው ህይወት ያልፋል፡፡


“ሴቶች እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ”



”ኤች አይ ቪ. ኤድስ” በሴቶች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም፤ በተለይም በደሃ ሀገራት ላይ የሚኖሩት ለቫይረሱ ያላቸው የተጋላጭነት ዕድል ሰፊ ነው። ለተጋላጭነታቸው ዋነኛ ምክንያት የቫይረሱ ሥነ-ሕይወታዊ ባህሪ ብቻ ሳይሆን ሴቶች ያላቸው የመራቢያ አካል ሥነ-ተፈጥሮ /Anatomical Structure/፣ኢኮኖሚያዊ አቅም እንዲሁም የሚኖሩበት ሀገር ፖለቲካዊ ሁኔታ ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ።

የሴቶች የመራቢያ አካል ሥነ-ተፈጥሮ /Anatomical Structure/ ከወንዶች ይልቅ ለቫይረሱ ያላቸውን የተጋላጭነት መጠን ከፍተኛ እንዲሆን ያደርጋቸዋል፡፡ ይሄም ሲባል ሴቶች በተፈጥሯቸው ዘር ተቀባይ እንደመሆናቸው መጠን የወንድ የዘር ፈሳሽ ውስጥ ያለ ቫይረስ ወደ ሰውነታቸው በቀላሉ የመግባትና የመቆየት ዕድል ስለሚኖረው በበሽታው የመያዝ ዕድላቸውን ይጨምረዋል፡፡ በተጨማሪም በሴቶች የመራቢያ አካል ውስጥ በሚፈጠሩ ቁስለቶች ወይም ስንጥቃቶች በኩል ቫይረሱ ወደ ደም ዝውውር ሥርዓቱ በቀላሉ የመግባት ዕድል ያገኛል፡፡

የሴቶች ኢኮኖሚያዊ ጥንካሬ ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንደሚያስገኝላቸው እሙን ነው፡፡ በተለይም ደግሞ በራሳቸው የመወሰንና የፈቀዱትን የማድረግ አቅም ያጎናፅፋቸዋል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ የራሷ ኢኮኖሚያዊ ገቢ የሌላትና በሌሎች ጥገኛ የሆነች ሴት ሕይወቷን ለመምራት እንዲሁም ለኑሮ አስፈላጊ የምትላቸውን ነገሮች ለማሟላት ስትል ፈቃዷ ባልሆነና ባላመነችበት የሕይወት ጎዳና ለመጓዝ ትገደዳለች፡፡

ለብዙ ሴቶች አቋራጭና ቶሎ ኢኮኖሚያዊ ጉድለቶቻቸውን ሲሞሉ ከሚመርጧቸው መንገዶች መካከል ቀዳሚው ወደ ወሲብ ንግድ መግባት ነው፡፡ በእርግጥ በፈቃዳቸው ሳይሆን ተገደው በሚገቡበት በዚህ ሕይወት ከሚገጥሟቸው ብርቱ ፈተናዎች መካከል የመደፈርና ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነት የመፈፀም ግዴታ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ከዚህ አለፍ ሲልም ከችግሯ በላይ የሚያስጨንቃት ነገር ባለመኖሩ በራሷ ላይ የመወሰን መብቷን ገንዘቡን ይዞላት ለሚመጣው ደንበኛዋ የመሸጥ ግዴታ ውስጥ ትገባለች፡፡ በዚህም ገንዘብ ለማግኘት ስትል ጥንቃቄ የጎደለው የወሲብ ግንኙነት ከማታውቀው ሰው ጋር ለመፈፀም ትገደዳለች፡፡

በሀገራት ውስጥ የሚኖር ፖለቲካዊ አለመረጋጋቶች ወደ እርስ በእርስ ግጭቶች የማደግና ለማሕበረሰብ ሥርዓት አልበኝነት መፈጠር ምክንያት ሲሆኑ ይታያሉ፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ የማሕበረሰቡ ዋነኛ አካል የሆኑትን ሴቶች ለፆታዊ ጥቃት እንዲጋለጡ ያደርጋቸዋል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ በሴቶች ላይ ከሚደርሱ ዋነኛ ጥቃቶች መካከል ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው ወሲባዊ ጥቃት ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በሴቶች ላይ የሚከሰተው ወሲባዊ ጥቃት ጥንቃቄ የጎደለው በመሆኑ ለኤች አይ ቪ. ኤድስ እንዲጋለጡ ያደርጋቸዋል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያት ውጭ ሴቶች የሚኖራቸው የተቃራኒ ፆታ ግንኙነት ልምምድ፣ የሚሠሩበት የሥራ ሁኔታ እና የሚኖሩበት አካባቢ በቫይረሱ የመያዝ ዕድላቸውን ከሚያሰፉ ተጨማሪ ምክንያቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በትዳር ውስጥ የሚገኙም ሆኑ ጓደኛ ያላቸው ሴቶች ያላቸው የወሲብ ሕይወት ለኤች አይ ቪ. ኤድስ ያላቸውን ተጋላጭነት ይወስናል፡፡ ይሄንንም ከሁለት ወገን መመልከት ይቻላል፡፡ አንደኛው ሴቶቹ ለሕይወት አጋራቸው ታማኝና ተወስነው የሚኖሩ አጋራቸው ግን ከብዙ ሴቶች ጋር ልቅ የሆነ ግብረ ስጋ ግንኙነት የሚፈፅም ሲሆን ነው፡፡

ይሄ ዓይነቱ ድርጊት ኢ-ሞራላዊና በየትኛውም ዓይነት ማህበራዊ መለኪያዎች ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም ባሻገር ለአጋሮቻቸው ታማኝ የሆኑትን ሴቶች ለኤች አይ ቪ. ኤድስ ተጋላጭ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ ያለውን ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን ራሳቸው ሴቶቹ ከትዳር አጋራቸው ወይም ጓደኛቸው ውጪ በሚፈፅሙት ጥንቃቄ የጎደለው ወሲባዊ ግንኙነት የሚፈጥርባቸው ተጋላጭነት ነው፡፡ በዛም ሆነ በዚህ በጥንዶች መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት በመተማመንና በመወሰን አለፍ ሲልም ኃላፊነት በተሞላ አኳኋን መሆን ይገባዋል፡፡

ሴቶች ኑሯቸውን ለማሸነፍ ሲሉ ከሚሠሯቸው ሥራዎች መካከል ደግሞ በተለይም በመስተንግዶ፣በማሳጅ ቤቶች፣ በምሽት ክበቦች እና በመሳሰሉት አካባቢዎች አብዛኛውን ጊዜ በጥቅም በመታለል፣ በመጠጥና በአደንዛዥ ዕፆች በመገፋፋት ላልተፈለገና ልቅ ለሆነ ወሲባዊ ግንኙነት ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ በእርግጥ በእነዚህ ቦታዎች የሚሠሩ ሴቶች በጠቅላላ በእንደነዚህ ዓይነት ህይወት ውስጥ ያልፋሉ ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን የቀን ተቀን ሕይወታቸው በዙሪያቸው ካለው ገፊ ምክንያት ጋር ተደምሮ በሚገጥማቸው ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ታግሎ ለማለፍ ከባድ ያደርግባቸዋል፡፡

በተመሳሳይም ከልጅነት ጊዜያቸው ጀምሮ ሴተኛ አዳሪ የሆኑ /በወሲብ ንግድ የሚተዳደሩ/ ሴቶች በብዛት በሚኖሩበት አካባቢ ወይም ከቅርብ ቤተሰቦቻቸው መካከል በዚህ ሥራ ውስጥ ሲሳተፉ እየተመለከቱ የሚያድጉ ሴቶች ይህን ህይወት ለመቀላቀል እምብዛም አዲስ ሲሆንባቸው አይስተዋል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ለዓመታት ሲመለከቱ የሚያዩት ነገር ልክ ነው ብሎ ለመቀበል ከሌላው ይልቅ ቀሎ ይታያቸዋልና ነው፡፡

ሴቶችን ለኤች አይ ቪ ኤድስ አጋላጭ የሆኑ ሁኔታዎች እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት ግን አይደለም፡፡ ለምሳሌ የሴቶች አለመማር፣ የወንዶችን የበላይነት በሚያንፀባርቅና ከአንድ በላይ የትዳር አጋር እንዲኖራቸው በሚፈቅድ ባሕልና እምነት ውስጥ መኖር የሴቶችን ለኤች አይ ቪ ኤድስ ተጋላጭነትን ከሚያሳድጉ ሁኔታዎች መካከል ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ የሴቶችን የኤች አይ ቪ ኤድስ ተጋላጭነት መቀነስ የሚቻለው በዋናነት በሁለተናዊ መልኩ ማብቃትና በኢኮኖሚ ራሳቸውን የሚችሉበት አቅም መፍጠር ሲቻል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ማሕበረሰቡ ለሴቶች የሚሰጠውን ሁለንተናዊ ድጋፍ አጠናክሮ በመቀጠል፣ አሳሪና ጎጂ ልማዶችን እንዲሁም በሴቶች ላይ የሚደርሱ ዓይነተ-ብዙ ጥቃቶችን በመፀየፍ አጋርነቱን ማሳየት ይኖርበታል፡፡ እንዲህ ሲሆን ሴቶች አቅማቸውን ማሳደግ፣ ለመብታቸው መታገል፣ እንዲሁም ራሳቸውን ከጥቃት መከላከል የሚችሉበት ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፡፡ በመሆኑም ሁሉም የድርሻውን በመወጣት ሴቶችን ለቫይረሱ ያላቸውን ተጋላጭነት መዋጋት ይኖርበታል፡፡





# ልዩ ልዩ

## ወጣትነትና ኤች አይ ቪ/ኤድስ

ወጣትነት የራሱ የሆነ አካላዊ፣አዕምሮዊና ስሜታዊ ለውጦች የሚንፀባረቁበት ስሜቶችን ወደ ተግባር ለመለወጥ ውስጣዊ ግፊት የሚያይልበት ወቅት በመሆኑ ጊዚያዊ ስሜቶች የወደፊት አላማን በአግባቡ ለማሳካት መሰናከል የሚሆኑበት ነው፡፡

ወጣቶችን ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ከሚያጋልጡ ሁኔታዎች ውስጥ  የግንዛቤ ማነስ፣ከአንድ በላይ የፍቅር ጓደኛ መያዝ፣ አልኮልና አደንዛዥ ዕፅ መጠቀም፣ በአጋጣሚ ከሚያገኙት ሰው ጋር ወሲብ መፈጸም፣ህገ-ወጥ ውርጃዎችን መፈጸም፣የጤና አገልግሎቶችን አለመጠቀም፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እና ከቦታ ቦታ መዘዋወር /ፍልሰት/ እና የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የተባበሩት መንግስታት ዘገባ እንደሚያሳየው ከሆነ እድሜያቸው ከ15 እስከ 24 ዓመት የሚጠጉ ከሰሐራ በታች የሚኖሩ ወጣቶች ዘንድ የቫይረሱ ስርጭት ከመቀነስ ይልቅ በየጊዜው እየጨመረ ይገኛል። ኢትዮጵያም ከሰሀራ በታች የምትገኝ ሀገር የመሆኗን ያህል ወጣቱ ለቅፅበትም ቢሆን ከኤድስ አማጪው ቫይረስ ራሱን ከመጠበቅ መዘናጋት የለበትም። ስለዚህ የዚህን አስከፊ በሽታ ለመከላከል 3ቱን የ”መ” ህጎች ተግባራዊ ማድረግ ነው ተገቢ ነው፡፡

### ሱስና መዘዙ

### ሱስ ምንድነው

በምንኖርበት ዓለም ላይ ሊያነጋግሩና ሊያወያዩ የሚችሉ በርካታ ኢ-ግብረገባዊ ድርጊቶች ተበራክተው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ኢ-ግብረገባዊ ድርጊቶች ከሰብዓዊነት የሚያወጡ ማህበራዊ ቀውስ የሚያስከትሉና ሀገራዊ ኪሳራ የሚያስከትሉ ናቸው፡፡

መቀመጫውን በካናዳ ያደረገው /CAHM/ የተባው የጥናት ተቋም ሱስ ማለት ልማድ፣ ጠባይ ወይም ብዙ ጊዜ ለማቆም አስቸጋሪ የሆነ እና በሰው ልጅ ሕይወት ጣልቃ የሚገባ እንደሆነ አስረድቷል፡፡

ከብዙ ጥናቶች መገንዘብ እንደምንችለው ሱስ ማለት ተደጋግሞ እንዲወሰድ የሚገፋፋ መጥፎ ልማድ ወይም ሁኔታ ሆኖ በሰዎች ላይ አካላዊና ሥነ-ልቡናዊ የጥገኝነት ስሜት በመፍጠር ለማነቃት፣ ድብርትን ለማስወገድ፣ ጀብድ ለመሥራት፣ ጊዜን ለማሳለፍ፣ ሕመምን ለማስታገስ፣ ከፍተኛ የደስታን ስሜት ለመጎናጸፍ በሚል ምክንያት ይወሰደል፡፡

እነዚህም የሚጨሱ፣ በአፍንጫ የሚወሰዱ/ የሚሳቡ/፣ በደም ስር ሚወሰዱ ነገሮችንም ሚያጠቃልል ሲሆን በተለይ ጤናማ የሚባል የአኗኗርን መንገድ የሚገድብና ከሰው ተራ የሚያወጣ ክፉ ልማድ ነው፡፡

በዓለም ላይ ለክፉ ልማድ በሚዳርጉ አደንዛዥ ዕፆች ምክንያት የተለያዩ ገደቦች እና ቅጣቶች ብናይም በሀገራችን ግን ከወጡ ሕጎች አፈጻጸም ጉድለት የተነሳ ከጊዜ ወደ ጊዜ መስፋፋቱ ትንሽ ግር ይላል፡፡

ከጦር መሳሪያ በላይ ሰውን ሳይተኩስ የሚገለው ዕጽ እንዲህ በይፉ ሰውን ሲያደነዝዘው አለመከላከል በትውልድ እና በሀገር ላይ ጉዳት ያመጣል፡፡ በእኛ ዘመን በታዳጊና ወጣቱ አካባቢ ጫት መቃም፣ ሲጋራ ማጨስ፣ በአልኮል መጠጦች ራስን መዝፈቅ እንዲሁም ሌሎች አደንዛዥ ዕፆችን መጠቀም ዘመናዊነት እና የስልጣኔ ምልክት አድርጎ መውሰድ የአደባባይ ምሥጢር ሆኗል፡፡

ክፋትን፣ ዐመጽን፣ ርኩሰትን፣ ከንቱነትን፣ ራስን ማጣትና ማጥፋትን የሚጸየፍ ትውልድ በድፍረት የሚቃወምና የሚገስጽ እንዴት ይታጣል? ወጣትነታችንስ እንዴት ሱስን መጸየፍ የሚችልበትን ኃይል አጣ? ነገሩን ከበድ የሚያደርገው ደግሞ የሱስ አጣቃቀም መንገድ እየሰፋና እየረቀቀ መሄዱ ነው፡፡ ክፉ ልምምድ የሚያመጡ ዕፆችን መጠቀም ኢ-ግብረ ገባዊ ከመሆኑም አልፎ በተለይ ዕፆችን ቀላቅሎ መጠቀም ጉዳቱን የከፋ ያደርገዋል፡፡

ለሱስ ሚያጋልጡ ነገሮች ብዙ ቢሆኑም ቀዳሚውን ስፍራ የያዘው ግን መገናኛ ብዙሃን ነው፡፡ ይህም በምስል፣ በጽሑፍ፣ በየዘፈኑ ክሊፕ በተደጋጋሚ ሲታይ የመለማመድ ፍላጎት ጫና ውስጥ ሲከት ይታያል፡፡ በተለይ የሚያስከትለውን ጉዳት ያልተረዱና ያልበሰሉ ወጣቶች የሚያደንቋቸውን የፊልም ተዋናዮች ዘፋኞችን ለመምሰል በሚደረግ ሙከራ ለሱስ መጋለጥ የተለመደ ነው፡፡ ለሱስ የሚያጋልጡ ነገሮች ሲነሱ ሊዘነጋ የማይገባው ነገር በቅርብ ወዳጆችና ጓደኞች ግፊት አማካኝነት በጥቂት ልምምድ፣ ስራ ፈትነት፣ ያለ ቦታ መገኘት ይነሳል፡፡

ስለሆነም በሱስ መንገድ እየተጓዙ፤ በሱስ ተጠምደው ወደ ውድቀት፣ ጉዳትና ራስን ወደ ጎጂ የህይወት አዙሪት በመክተት ህይወትን ሊያውክና የተረጋጋ ኑሮ እንዳይኖር ከሚያደርጉ ለሱስ የሚያጋልጡ ቦታዎች እና ሰዎች ዘንድ መራቅ ብልህነት መሆኑን እንወቅ፡፡

## ሱስ በወጣቶች ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ

ሱስ ስንል ማንኛውም ነገር በሰዎች ላይ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጥገኝነት ስሜት በመፍጠር ሰዎች ለመነቃቃት፣ ድብርትን ለማስወገድ፣ ጀብዱ ለመሥራት፣ ህመምን ለማስታገስና ከፍተኛ የደስታ ስሜትን ለመጎናጸፍ ብለው የሚያጨሷቸው፣ የሚቅሟቸው በአፍንጫ የሚስቧቸውንና በደም ስር የሚወስዷቸውን ነገሮች በሙሉ ያካትታል።

ያለ እነኚህ ሱሶች/ዕፆች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴአቸውን ማከናወን ሲሳናቸው ሱስ ወይም የሱሰኝነት ጠባይ እንዳላቸው ይገለጻል፡፡ ሰዎች ከላይ ከተገለጹት ዕውነታዎች በተጨማሪ ሱስ የሚያሲዙ ነገሮችን በተለያዩ ምክንያቶች ይጠቀማሉ፡፡ ከእነኚህም የጓደኛ፣ የቤተሰብና የአካባቢ ተጽንኦ እንደ ዋንኛ ምክንያት ተደርጎ ይጠቀሳል፡፡ እንደ ቀልድ አንድ ብለው የጀመሩት ሲውል ሲያድሩ አንድ የህይወታቸው አካል ይሆንና ህይወታቸውን በማመሰቃቀል እስከ ህይወት ህልፈት ሊያደርሳቸው ይችላል፡፡

በተለይ ሱስ አምራች ኃይል በሚባሉት ወጣቶች ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ቀላል አይደለም፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ ብዙ ወጣቶች ያሏት እንደመሆኗ ወጣቱ በሱስ የተያዘ ከሆነ የአገሪቱ መጻኢ ዕድል የተንሰራፋ ድህነት፣ኋላ ቀርነት፣ወንጀልና ለሀገር ሸክም የሚሆን ዜጋ ስለሚኖር በቀጣይ ጤናማ ትውልድ ማፍራት አዳጋች ይሆናል፡፡ ወጣቶች ለረጅም ጊዜ በሱስ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ ብዙ ችግሮችና ተግዳሮቶች በፊታቸው ይደቀኑባቸዋል፡፡ ከዚህ የሚከተሉት ነጥቦች ወጣቶች ሱስ ውስጥ በመግባታቸው ምክንያት የሚከሰቱ ተጽዕኖዎች ናቸው፡፡

## ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ

በሱስ ለተጠመዱ ወጣቶች የሚወጣው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ወጪ ቀላል አይደለም፡፡ በሱስ በመጠመዳቸው ምክንያት እራሳቸውን ማስተዳደር ስለማይችሉ በሌሎች ላይ ጥገኛ ይሆናሉ፡፡ ከፍ ሲልም

የሚያገኙትን ገንዘብ ሁሉ ሱሳቸውን ለማስታገስ ይጠቀሙበታል። ያን ማድረግ ካልቻሉ ደግሞ ወደ ወንጀል ሊሰማሩ ይችላሉ፡፡ ይህም በመሆኑ ከሱስ ውስጥ እንዲወጡ ለማድረግ የሚደረገው የህክምና ዕርዳታ ቀላል የማይባል ወጪ ያስወጣል፡፡

## አዕምሯዊ ጤና ድብት

የዕድገት ውስንነት፣ ተስፍ መቁረጥ፣ መገለል፣ ስነ-ልቦናዊና ማኅበራዊ ችግሮች ከሱሰኝነት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አላቸው፡፡ በሱስ የተጠመዱ ወጣቶች ከሱስ ነፃ ከሆኑ ወጣቶች ጋር ሲነጻጸሩ ለተለያዩ የአዕምሮ በሽታዎች የመጋለጥ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ ድብርት፣ አስቸጋሪ ጠባይ፣ የስብዕና መቃወስ፣ እራስን ለማጥፋት ማሰብና መሞከር እንዲሁም ማጥፍት ተጠቃሽ ናቸው፡፡በተጨማሪም ሱስና አደንዛዥ ዕፅ የወጣቶችን የማስታወስ ስርዓት፣ስነ-ልቦናዊና አካላዊ ክህሎቶችን ያዛባል፡፡

## የወጣት ጥፋተኝነት



ዕድሜቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶች ወንጀል ቢሠሩ እንኳን ወንጀለኞች ሳይሆን ወጣት ጥፋተኞች ነው የሚባሉት፡፡ ማንኛውም ሰው ሊክደው የማይችል የወጣት ጥፋተኝነትና ሱስ ግንኙነት አላቸው፡፡ በሱስ ምክንያት ወጣቶች የተለያዩ ጥፋቶችን ሲያጠፉ በፍርድ ቤት ጉዳያቸው ተመርምሮ ጥፍተኛ ሆነው ከተገኙ ወደ ወጣቶች ተሐድሶ ማዕከል እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ ሱሰኝነት ወጣት ጥፋተኝነትን፤ወይም ወጣት ጥፋተኝነት ሱሰኝነት አያስከትልም። ነገር ግን አንዱ የአንዱ ምክንያትና ውጤት መሆን ባይችሉም ቁርኝነት አላቸው። በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ ወንጀል፤ ማኅበራዊ ቀውሶች ከሱስ ጋር የመያያዝ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡

## በአካላዊ ጤና

አብዛኛውን ጊዜ በከተሞች አካባቢ የሚታዩት አደጋዎች ለምሳሌ የመኪና፣የአካል ጉዳትና የተለያዩ በሽታዎች (ተላላፊ በሽታዎች ኤች አይቪ/ኤድስን የመሳሰሉት) በወጣቶች ላይ የሚከሰቱት በሱስና አደንዛዥ ዕፅ ምክንያት ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የመኪና አደጋዎች መንስኤቸው ጠጥቶ ማሽከርከር ነው። አብዛኛውን ጊዜ አሽከርካሪዎቹም ወጣቶች ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት በንብረት ላይ ጉዳት ከማድረስ ባሻገር ለአካል ጉዳተኝነትና ለሞት የተጋለጡ ናቸው፡፡

## በትምህርት

በተማሪ ወጣቶች ላይ የውጤት ማሽቆልቆል፤ ከትምህርት ቤት መቅረትና ሌሎች እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳታፊ አለመሆን፤ እንዲሁም ትምህርት ማቋረጥ፤በሱስ ውስጥ ያሉ ወጣቶች የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ናቸው። ይህም የሚሆንበት ምክንያት አደንዛዥ ዕፅና ሱሰኝነት በአዕምሯቸውና በጠባያቸው ላይ በሚያሳድረው ተጽዕኖ ትምህርታቸውን በትኩረት መከታተል እንዳይችሉ ስለሚያደርጋቸው ነው፡፡

በጓደኝነት

በሱስ ውስጥ ያሉ ወጣቶች ከጓደኞቻቸው ወይም አቻዎቻቸው መገለል ይገጥማቸዋል፡፡እንዲሁም በሱስ የተያዘ ጠባያቸውን በመመልከት ማኅበረሰቡ የተለያዩ አካባቢያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሌሎችንም ያበላሻሉ ብሎ በማሰብ እንዳይሳተፉ ይከለክሏቸዋል። ይህም ለለውጥና እራሳቸውን ለመቀየር ያላቸውን መነሳሳት ያኮላሸዋል፡፡

## በቤተሰባዊ

ሱሰኝነት ከግላዊ ተግዳሮቶች ባሻገር በቤተሰብ ህይወት ውስጥ ትልቅ ችግር ይፈጥራል፡፡በተለይ በወንድምና እህቶች ላይ የሚፈጥረው ጫና ቀላል የሚባል አይደለም አይደለም፡፡ ወንድማቸው /እህታቸው ወይም አንድ የቤተሰብ አካል በሱስ መጠመዱ በጓደኞቻቸውና በማኅበረሰባቸው ውስጥ ከመልካም ቤተሰብ እንዳልመጡ አድርጎ ስለሚመለከታቸው ከሌላው ጋር ማኅበራዊ መስተጋብር ለመፍጠር ይሸማቀቃሉ። እራሳቸውንም ያገላሉ፡፡

## ከሱሰኝነትን እንዴት መላቀቅ ይቻላል?

1. የመድኃኒት ህክምና

የመድኃኒቶች ህክምና በሱስ የተያዙ ሰዎች ሰውነት ውስጥ የተከማቹትን መርዛማ ኬሚካሎችን ማስወገድን ያካትታል፡፡

2. ስነ-ልቦናዊ ህክም

ማንኛውም ለውጥ ከአእምሮ ይጀምራል እንደሚባለው በሱስ ውስጥ ያሉ ሰዎች በምክር አገልግሎት ሰጪ ባለሙያ በመታገዝ ከሱስ ለመውጣት ስነ-ልቦናዊና አእምሮአዊ ዝግጅትና ቁርጠኝነት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስለዚህ ስነ-ልቦናዊ ህክምና በሱስ የተያዙ ሰዎችን ስነ-ልቦና በማጠንከር የሱስ ጥገኝነትን ለማስወገድ ትልቅ ድርሻ አለው፡

3. መጠንን መቀነስ

አብዛኛውን ጊዜ ሱስ ያለባቸው ሰዎች ሱሰኝነትን ለመተው ያስቡና ሁሉንም ነገር በአንድ ጊዜ ለማቆም ይሞክራሉ፡፡ ይህ እርምጃ ምንአልባት ለአንድና ለሁለት ቀን ያገለግል እንደሆን እንጂ ዘለቄታዊ መፍትሄን ማምጣት አይችልም፡፡ ሱሰኝነትን በአንድ ጊዜ ወይም በቅጽበት ለመተው ከማሰብ ይልቅ መጠንን እየቀነሱ ለዘለቄታው እስከመተው መድረስን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡





የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት

Ethiopian Electric Utility